# በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

## የጎብኚዎች ደህንነት መመሪያ ቁጥር 808/2013

ነሐሴ 14 ቀን 2013 ዓ.ም

# መመሪያ ቁጥር 808/2013
# በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
# የጎብኚዎች ደህንነት መመሪያ

በዓለም አቀፍ ደረጃ ባልተለመደ ሁኔታ በተቀሰቀሰው የበሽታ ወረርሽኝ በቱሪዝም ዘርፉ ላይ የደቀነው አደጋ በተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች እና በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ እያስከተለ በመሆኑ፤

በኮቪድ 19 ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ ምክንያት መንግስታት የወሰዱትን ፈጣንና ጠንካራ እርምጃዎች ተከትሎ ገደብ ተጥሎባቸው የነበሩ የጉብኝት እንቅስቃሴዎች ቀስ በቀስ እየላሉና በበርካታ የቱሪስት መዳረሻዎች የቱሪዝም እንቅስቃሴዎችን በድጋሚ እየተጀመሩ በመሆኑ፤

ሀገራችን ኢትዮጵያ የቱሪዝም እንቅስቃሴዎች ደህንነታቸው በተጠበቀ እና ሃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ በማስተዳደር ለማስጀመር እንዲያስችል በዓለም አቀፍ ደረጃ የተዘጋጀውን ደህንነቱ የተጠበቀ የጉብኝት ፕሮቶኮል እና የአሰራር ስርዓት መቀበል አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ፤

የጎብኚዎችን እምነት በድጋሚ ለመገንባት እና የቱሪዝም ዘርፍ እሴት ሰንሰለት ውስጥ የተሰማሩ ሰራተኞች የጤና ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ግልፅ፣ ወጥ እና ፍትሐዊ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት በማስፈልጉ፤

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀፅ 30 የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች በአግባቡ ለመወጣት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ “የጎብኚዎች ደህንነት መመሪያ ቁጥር 808/2013” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>**ትርጓሜ**</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመርያ ውስጥ፡-

1. **"የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት"** ማለት ሆቴሎች፣ ሎጆች፣ ሬስቶራንቶች፣ የእንግዳ ማረፊያዎች፣ አስጎብኚ ድርጅቶች እና ሌሎች ለጎብኚዎች በቀጥታ ምርትና አገልግሎት የሚያቀርቡ ድርጅቶች ማለት ነው።
2. **"የሆስፒታሊቲ ተቋማት"** ማለት ለጎብኚዎች በክፍያ የምግብ፣ የመጠጥ፣ የመኝታ፣ ማረፊያ እና ልዩ ልዩ የመዝናኛ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች ናቸው።
3. **"ደህንነቱ የተጠበቀ የጉብኝት ፕሮቶኮል"** ማለት የጎብኚዎችን፣ የዱር እንስሳትን፣ የአካባቢውን ማህበረሰብ እና በዘርፍ የተሰማሩ ባለሙያዎችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከኮረና እና መሰል ተዛማጅ ወረርሽኞች ለመጠበቅ ከፍተኛ የደህንነት ደረጃዎችን ለማስጠበቅ የተነደፉ የጉዞ እና የቱሪዝም ኢንዱስትሪ የተለመዱ እና ልዩ የደህንነትና ንፅህና መመዘኛዎች ናቸው፡፡
4. **"የጉዞ ደህንነት ማረጋገጫ"** ማለት ለጉዞና ቱሪዝም ዘርፍ በዓለም የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ የደህንነትና ንጽህና ማረጋገጫ ማህተም ሲሆን ይኸውም በተለይ በተጓዡ በኩል በኮረና ቫይረስና መሰል ወረርሽኞች ያለውን ስጋት ለማስወገድ ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡
5. **"መስህቦች"** ማለት በአለም አቀፍ ወይም በአገር ውስጥ ቱሪስቶች ለመዝናናት፣ ለስብሰባና ለቢዝነስ፣ ለምርምር እና ለሌላ ማንኛውም የቱሪዝም ዓላማዎች የሚዘወተሩ ተፈጥሮአዊ ፣ ባህላዊ እና ታሪካዊ መስህቦችን ያጠቃልላል፡፡
6. **"ሚኒስቴር"** ማለት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ነው፡፡
7. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
8. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው አነጋገር የሴትንም ጾታ ይጨምራል፡

3. <u>**ዓላማ**</u>

<u>**የዚህ መመሪያ ዓላማ**</u>

1) በጉብኝት ሥርዓት የሚሳተፉ አካላትን ደህንነት ለማረጋገጥ ዓለም አቀፍ የጉዞና የቱሪዝም ደህንነትና ጤና መለኪያ ፕሮቶኮሎችን በመተግበር ኢትዮጵያን የድህረ ኮረና የጉብኝት መዳረሻ ማድረግ፣

2) በኮሮና ወረርሽኝ የተስተጓጎለውን የአገሪቱን የቱሪዝም እንቅስቃሴን በከፍተኛ ጥንቃቄና ኃላፊነት በመደገፍ የቱሪዝም ኢኮኖሚው እንደገና እንዲነቃቃ በማድረግ ተወዳዳሪነትን ማሳደግ፣

4. **<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

1) ይህ መመሪያ በሀገሪቱ በሚገኙ የቱሪዝም መዳረሻዎች፣ የቱሪስት አገልግለቶች ሰጪ ተቋማት፣ በተለያዩ የቱሪዝም አገልግሎቶች እና በቱሪስቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፣

2) ይህ መመሪያ የዓለም ጤና ድርጅት እና በጤና ሚኒስቴር በሚወጡ ህጎች እና ሌሎች አቅጣጫዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ ይፈፀማል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>ስለቱሪዝም አገልግሎት ሰጪ ተቋማት</u>
## <u>ተግባርና ኃላፊነት</u>

5. **<u>የወል ተግባርና ኃላፊነቶች</u>**

ሁሉም የቱሪዝም አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አገልግሎታቸውን ለደንበኞቻቸው ከመስጠታቸው በፊት የሚከተሉትን ዝርዝር ሁኔታዎች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡-

1) የሚሰጡትን አገልግሎት ጥራትና አሰጣጥ ከፍተኛ መሆኑን የማረጋገጥና ይህንኑ አገልግሎት አሰጣጥ የሚተገብሩና የሚያቅዱ የሰለጠኑ ሰራተኞችን የማሟላት፤

2) የኮረና ቫይረስ መከላከያ የድርጊት መርሃ ግብር፣ ቼክ ሊስት፣ ልዩ የጽዳትና የዲስ ኢንፌክሽን አሰራርን አካቶ የያዘ ዕቅድ የማዘጋጀት፤

3) ሰራተኞቻቸውና ደንበኞቻቸው በዓለም ጤና ድርጅትና በጤና ሚኒስቴር የፀደቁና የተሰጡ የምክረ ሃሳብ ፕሮቶኮሎችና መመሪያዎች እንዲያከብሩ የማድረግ፤

4) በአንድ ጊዜ የሚገቡ ሰራተኞቻቸውን እና የደንበኞቻቸውን ቁጥር በመመጠን አገልግሎት በሚሰጡባቸው ማዕከሎችና የቢሮ አቀማመጣቸው አካላዊ ርቀትን እና ንክኪን የሚቀንሱ እንዲሆኑ የማድረግ፤

5) ለድርጅቱ ሰራተኞች የበሽታ መከላከያ መሳሪያዎች (PPE) የፊት ጭብልና ጓንት በተገቢው ደረጃ የማሟላት፤

6) ከእጅ ንክኪ የፀዳ የገንዘብ መቀበያ ዘመናዊ አሰራር የመተግበር፤ ካልተቻለ ጓንት እና የእጅ ንፅህና መጠበቂያ ሳኒታይዘር የማቅረብ፤

7) አዳዲስ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ከአቅራቢዎች እና ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር የኮቪድ -19 አስቸኳይ ጉዳዮችን ማስፈጸሚያ እቅድ (Contingency Plan) የማዘጋጀት፤

8) የስራ ቦታቸውንና ለተገልጋዮቻቸው አገልግሎት የሚሰጥባቸውን ቁሶች ተገቢውን የጥራት ደረጃ የጠበቀ የፀረ ተህዋሲያን እርጭት የማከናወን፤

9) ለሰራተኞቻቸው ስለኮቪድ 19 ወረርሽኝ ተገቢውን የግንዛቤ ማስጨበጫ የመስጠትና የመከላከያ መንገዶቹን እንዲተገብሩ ተገቢውን ድጋፍ የመስጠት፤

## 6. <u>የአስጎብኚ ድርጅቶች ተግባርና ኃላፊነቶች</u>

የዚህ መመሪያ አንቀፅ 5 እንደተጠበቀ ሆኖ አስጎብኚ ድርጅቶች አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

1) በአዲስ መልክ ተግባራዊ የተደረጉ የደህንነት እርምጃዎችን ለደንበኞቻቸው የማሳወቅ፤

2) ለጎብኚዎች የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡባቸውን ተሽከርካሪዎች ንፅህና፣ የፀረ ተዋሲያን ርጭት እና ጥልቅ ፅዳት ተግባሮችን የማሳደግና አገልግሎት በሰጡ ቁጥር ይህንኑ የመተግበር፤

3) ከጤና ተቋማት እውቅና የተሰጣቸውን የፀረ ተህዋሲያን መርጫ ምርቶችን የመለየትና የመጠቀም፤

4) የንፅህና አገልግሎት ሰጪ ቡድኖች የእጅ መገልገያዎችን፣ የበር እጄታዎችን፣ ጠረጴዛዎችን፣ መጸዳጃ ቤቶችን፣ የአየር ማቀዝቀዣዎችን፣ የመኪና እቃ ማስቀመጫዎችን፣ የጆሮ ማዳመጫዎችን ጨምሮ በከፍተኛ ሁኔታ በተደጋጋሚ ለንክኪ ተጋላጭ የሆኑ ቦታዎች ልዩ ትኩረት በመስጠት ቶሎ ቶሎ እንዲያፀዱ ተገቢውን አቅጣጫ የመስጠት፤

5) ተጨማሪ የግል የፀረ ተህዋሲያን ምርቶች ለጎብኝዎች ማቅረብ ወይም በክፍያ ተደራሽ የሚሆኑበትን ሁኔታ የማመቻቸት፤

6) በንፅህና መጠበቂያ ቦታዎች ላይ ተቀባይነት ያላቸውን በአልኮል የተሰሩ የእጅ ሳኒታየዘሮችን ተደራሽ የማደረግ፤

7) በተሽከርካሪ ውስጥ ቦታ መቀያየርን የማይፈቅድ የቦታ አቀማመጥ ድልድል ማውጣት፣ በብሔራዊ ፕሮቶኮል መሠረት የመቀመጫ ቦታ ክፍተትን የመተግበር፤

8) ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫቶችን ተደራሽ ማድረግና ቆሻሻዎች በመደበኛ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች ብቻ ማስወገድ፣
9) በሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊና አስገዳኝ ሆኖ ሲገኝ የእንግዶች የጤና ሁኔታ ቁጥጥርና ምርመራ የመተግበር፤ በተቻለ መጠን አካላዊ ጥግግትን እና ወረፋ መቀነስ፤
10)ለእንግዶች ወደ መኪና ሲገቡ እና ሲወጡ  የፊት መሸፈኛ ጭምብልና ሳኒታይዘር ተደራሽ የማድረግ፤
11)ከእንግዶች ጋር ከንክኪ ነፃ የሆነ ግንኙነትና ሰላምታ ስርዓቶችን የመተግበር፣
12)በሚደርሱበት ስፍራ ከጤና ማዕከላት እና ከፖሊስ ጣቢያዎች ከተቻለም ከጤና እና የጉዞ መድን ኩባንያዎች ጋር የመቀናጀት፤
13)ግልፅ፣ የማይቋረጥ እና ወቅታዊ የጤና እና የንፅህና መመምሪያዎችን በዲጅታልና በአካል ለደንበኞች የማሳወቅ።

7. <u>የቱሪስት ትራንስፖርት ሰጪ አካላት ተግባርና ኃላፊነት</u>

የዚህ መመሪያ አንቀፅ 5 እንደተጠበቀ ሆኖ የቱሪስት ትራንስፖርት ሰጪ አካላት አገልግሎታቸውን ለጎብኚዎች ለመስጠት የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

1) የአካላዊ ንክኪ ላላቸው ክፍሎች ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ተሽከርካሪዎቻቸውን ጉዞ ከመጀመራቸውና ከጉዞ በኃላ በአግባቡ የማፅዳት፤
2) ጥቅም ላይ የዋሉ የንፅህና ቁሶችን እና ለግል አገልግሎት የዋሉ ቁሶችን በአግባቡ ጥብቅ ክዳን ባላቸው የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች የማስወገድ፤
3) በአሽከርካሪው እና ከኋላ በተቀመጡ ተሳፋሪዎች መካከል የሚለይ የፕላስቲክ ወይም የግላስ መከለያዎችን የመትከል፤
4) የእጅ ሳኒታይዘርና የፊስ ማስክን የመያዝና የመጠቀም፤
5) በጉዞ እና ከጉዞ በኋላ ጎብኚዎች በጤና ሚኒስቴር የወጡ የመከላከያ እርምጃዎችን እንዲያከብሩ የማድረግ።

8. <u>የሆስፒታሊቲ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት</u>

የዚህ መመሪያ አንቀፅ 5 እንደተጠበቀ ሆኖ የሆስፒታሊቲ ተቋማት አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

1) ሰራተኞቹ ወደ ተቋሙ ሲገቡ እና ሲወጡ ተገቢው የሙቀት ልኬት እንዲደረግላቸውና ሳኒታይዝ እንዲደረጉ የማድረግ፤
2) ሰራተኞቹ በአመት አራት ጊዜ የኮቪድ 19 ምርመራ እንዲያደርጉ የማድረግ፤
3) ሰራተኞቹ የጤና ምርመራ እንዲያደርጉ አስፈላጊ ሀብቶችን በማቅረብ ተገቢውን ድጋፍ የማድረግ፤
4) በተቋሙ ውስጥ ኬዞች በሚጨምሩበት ወቅት ለኢትዮጵያ የማህበረሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የማሳወቅ።

## 9. <u>የሆቴሎች ተግባርና ኃላፊነት</u>

የዚህ መመሪያ አንቀፅ 5 እና 8 እንደተጠበቁ ሆነው ሆቴሎች አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርባቸዋል፦

1) ለተገልጋዮቻቸው ተደራሽ የሚሆኑ ክፍሎችን በየቀኑ የማፅዳትና የፀረ ተህዋሲ ርጭት የማካሄድ፤
2) ለተገልጋዮቻቸው ተደራሽ በሚሆኑ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ እቃዎችን የማፅዳትና የፀረ ተህዋሲ ርጭት የማካሄድ፤
3) አገልግሎት በሚሰጥበት ወቅት ማህበራዊ ርቀትን በመጠበቅና ንክኪን በመቀነስ ደንበኞቻቸው የደህንነት እርምጃዎችን እንዲያከብሩ የማድረግ፤
4) በተደጋጋሚ ንክኪ የሚበዛባቸውን ቦታዎች ቶሎ ቶሎ በፀረ ተህዋሲያን ምርቶች የማፅዳት፤
5) አገልግሎት መስጫ እቃዎችን ሳኒታይዝ በማድረግ፣ የፊት ማስኮችን በማድረግ፣ የእንግዶችን ሰልፎች በመቀነስ ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ የምግብ አገልግሎቶች የመስጠት።

## 10. <u>የመዳረሻ ቦታዎች ተግባርና ኃላፊነት</u>

የመዳረሻ ቦታዎች የሚከተሉትን የመከላከያ እርምጃዎች ተግባራዊ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

1) ተገቢ የሆኑ ሳኒታይዘሮችን በመጠቀም በተደጋጋሚ የማፅዳትና ዲስ ኢንፌክሽን የማድርግ፤

2) ቋሚና ተንቀሳቃሽ የሙቀት መለኪያ አገልግሎት መስጫዎችን፣ መታጠቢያ ክፍሎችን፣ መፀዳጃዎችን እንዲሁም የእጅ መታጠቢያ ቦታዎችን በመግቢያ፣ በመንገድ እና መውጫ ቦታዎች ላይ የማዘጋጀት፤
3) በመዳረሻው ውስጥ ተገቢ የውሃ አቅርቦትና ተደራሽነት፣ የሳሙና እና ደረጃቸውን የጠበቁ ሳኒታይዘሮች መኖራቸውን የማረጋገጥ፤
4) በመዳረሻው ያሉ የጎብኚዎች መቆሚያ እና መቀመጫ ቦታዎችን የመመጠንና የመቆጣጠር፤
5) ጎብኚዎች በሚበዙባቸው ወቅቶች የተለያዩ የጉብኝት ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት፤ ወቅታዊ እና ጊዜያዊ የጎብኚዎችን ቁጥር የመመጠን፤
6) በአንድ ግሩፕ የሚገኙ የጎብኚዎች ቁጥር ከዘጠኝ እንዳይበልጥ፤ መገደብና ተገቢውን ማህበራዊ ርቀት የማስጠበቅ፤
7) ቱሪዝምን ለማስጀመር የማስታወቂያ ዋጋዎችን በማውጣት ተግባራዊ የማድረግ፤

## 11. <u>ቦታ ስለማስያዝ  እና የክፍያ ሥርዓት</u>

1) ተገልጋዮች አስቀድመው ቦታ እንዲያሲዙ በማድረግ የመዳረሻውን አቅም የማስተዳደር፤
2) ተጨማሪ አማራጭ የመግቢያ ሰዓቶችን (ጠዋት፣ ከሰዓት እና ማታ) ማዘጋጀት፤
3) በመዳረሻ ቦታዎች እና በክፍያ ማዕከሎች የሚኖሩ ሰልፎችን ማስወገድ፤ በሚቻልበት ጊዜ ሁሉ የባንክ ክፍያዎችን የመፈፀም፤
4) ከተለያዩ ባንኮች ጋር በመቀናጀት አነስተኛ ንክኪ ወይም ምንም አይነት ንክኪ የሌላቸውን የክፍያ አግባቦች የማመቻቸት፤
5) በትኬት ቢሮዎች የአገልግሎት ሰጪዎችን ቁጥር በመወሰን የክፍያ መስኮቶችን የመጨመር፤ በክፍያ እና ደረሰኝ መቀበል ወቅት የሚኖሩ ግንኙነቶችን የመቀነስ፤

## 12. <u>የሚኒስቴሩ ተግባርና ኃላፊነት</u>

ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1) የመመሪያውን አፈፃፀም በሁሉም የቱሪዝም አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የመከታተልና የመቆጣጠር፤
2) ለሚመለከታቸው አካላት ሙያዊ ምክሮችን በመስጠት የመከላከያ እርምጃዎቹ ተግባራዊ እንዲሆኑ የማበረታታት፤

3) የመከላከያ እርምጃዎቹን በሚጥሱ አካላት ላይ ተገቢውን አስተዳደራዊ እርምጃ የመውሰድ፤

4) በመመሪያው ላይ ለሚመለከታቸው አካላት ተገቢውን የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራትን የማከናወን፤ አፈጻጸሙን በየወቅቱ በመገምገም ተገቢውን አቅጣጫ የመስጠት፤

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 13. የአተገባበር ስልቶች

1) መመሪያው በዓለም ጤና ድርጅት፣ በመንግስት በሚወጡ ተዛማጅ ህጎችና መመሪያዎች፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በሚሰጡ ምክረ-ኃሳቦች የሚመራና የሚተገበር ይሆናል::

2) በመመሪያው ውስጥ የተቀመጡ መለኪያዎች አተገባበር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ጠንካራ የክትትል፣ ድጋፍ እና ጥብቅ ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል::

3) በሁሉም የቱሪዝም የዕሴት ሰንሰለት ውስጥ፣ በየደረጃው በሚገኙ ባለድርሻ አካላት እንዲሁም በየመዳረሻዎቻችን ቀላል፣ ሊተገበር የሚችል፣ ግልጽና የተቀናጀ አሠራር እንዲኖር ይደረጋል፣

4) መመሪያው ላይ በቂ ግንዛቤ ለመፍጠር የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች ከሙያ ዘርፍ ማህበራት ጋር በትብብር የሚከናወን ይሆናል፡፡

### 14. ክልከላ

1) ዝቅተኛ የማህበራዊ ርቀት እርምጃዎችን ተግባራዊ ያላደረጉ መዳረሻዎችን ለአገልግሎት መክፈት የተከለከለ ነው፤

2) በጤና ሚኒስቴር የወጡ የወረርሽኝ መከላከያ እርምጃዎችን መተላለፍ የተከለከለ ነው፡፡

### 15. የቅንጅት ዘዴዎች

ሁሉም የቱሪዝም አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ወረርሽኙን ለመከላከል አገልግሎታቸውን ሲሰጡ ከኢትዮጵያ የማህበረሰብ ጤና ኢንስቲትዩት እና ከአካባቢው የጤና ማዕከሎች ጋር በቅንጅት መስራት ይኖርባቸዋል።

16. <u>የጎብኚዎች የመተባበር ግዴታ</u>

1) ጎብኚዎች ከዱር እንስሳት ጋር መኖር የሚገባውን ዝቅተኛ የማህበራዊ ርቀት ማክበር ይኖርባቸዋል፤
2) ጎብኚዎች የዱር እንስሳትን ከመመገብ መቆጠብ ይኖርባቸዋል፤
3) ጎብኚዎች የሚጠቀሙባቸውን ቁሳቁሶች ከተፈጥሯዊ እና ከዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ላይ ከመጣል መቆጠብ ይኖርባቸዋል።

17. <u>ተያያዥ ህጎችና መመሪያዎችን ስለማክበር</u>

ሁሉም የቱሪዝም አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የወረርሺኙን መስፋፋት ለመቀነስ በሚያደርጉት ጥረት በጤና ሚኒስቴር የወጡ የተለያዩ ህጎችና መመሪያዎችን ማክበር ይኖርባቸዋል።

18. <u>አስተዳደራዊ እርምጃዎች</u>

1) ሚኒስቴሩ በመመሪያው የተቀመጡ የደህንነት እርምጃዎችን ጥሰው በሚገኙ አካላት ላይ እንደአግባብነቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተገቢውን አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፤
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ መሰረት የሚወሰደው እርምጃ ተቋሙን በጊዜዓዊነት አገልግሎት እንዳይሰጥ ከማገድ አንስቶ የስራ ፍቃድ እስከመሰረዝ ሊደርስ ይችላል፡፡

19. <u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህ መመርያ ሊያሻሽለው ይችላል፣

20. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ከነሐሴ 14 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ሂሩት ካሳው ወንድም (ዶ/ር)
የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
ሚኒስትር